# “ገንዘብ አላችሁ” ምንጩን ለሌላ ልቀቁ

ከጌታቸው ኃይሌ

ፕሬዚዴንት ኦባማ አዲስ አበባ ላይ ለተሰበሰቡት የአፍሪካ መሪዎች ሰኞ ዕለት ሐምሌ 20 ቀን 2007 ዓመተ ምሕረት ንግግር እንዳደረገላቸው እናስታውሳለን ። በንግግሩ ውስጥ ሥልጣን ለባለተራ የሚተው እንጅ እስከ ዕለተ ሞት የሚስገበገቡለት እንዳይደለ ለመሪዎቹ ሲያስታውሳቸው ገንዘብ እንደሆን አከማችታችኋል አላቸው ። አፍሪካውያንን በሥልጣን ኮርቻ ላይ ለመንጠላጠል ፥ ከተንጠላጠሉ በኋላም እዚያው ተጣብቆ ለመኖር የሚያጓጓቸው ገንዘብ ለመግፈፍ ብቻ ሊሆን አይችልም ። ይህ አንዱ ነው እንጂ ፥ ሁሉም አይደለም ። ለምሳሌ ፥ የደርግ ባለሥልጣኖች ለሥልጣኑ የተስገበገቡት ገንዘብ ለማካበት አይመስለኝም ። ባለሥልጣን መሆን ስም ያስጠራል ። አልባሌ ሆኖ ከመቅረት ያድናል ። ሥልጣን ለጎይለ ማርያም ደሳለኝ የጠቀመው ይኸ ብቻ ይመስለኛል ። በችሎታቸውና በሕዝብ ምርጫ የታላላቅ አገሮች መሪዎች ከሆኑ ጋር እኩል ይቆማል ፤ አብሮ ይበላል ። ከሰው ዓይንና ከሰው አፍ ላለመጥፋት ብዙ ሰዎች የቱን ያህል እንደሚጓጉለት በርሊን ከተማ ሄዶ ለሰፊ ሕዝብ በመታየት ራሱ መስክሯል ።

ገንዘብ ለማጋበስ ብቻ የሚደራጁና ከሥልጣን ላይ የወጡ ማፊያዎችና የትግሬ ወያኔዎች ብቻ ናቸው ። እነዚህ ሁለት ድርጅቶች በሁሉ ረገድ ሲመሳሰሉ በአንድ ነገር ብቻ ይለያያሉ ።

ማፊያዎችን መንግሥት በተቻለ መጠን ይቆጣጠራቸዋል ። ወያኔዎች ራሱን መንግሥቱን ተቆጣጥረውታል ። በሌላው ግን ጠባያቸው አንድ ነው ።

ማፊያዎች ያለውን ሁሉ በሞት እያስፈራሩ ይዘርፉታል ፤ ወያኔዎች መንግሥት ስለሆኑ ማንንም ሲቀሙ መንግሥት ስለሆኑ መንግሥት ይከታተለናል ብለው አይፈሩም ። አባቱ ዳኛ አባቱ ቀማኛ ።

ማፊያዎች የሚጠረጥሩትን ሲገድሉ ደንታ የላቸውም ። ወያኔዎች ምን ጊዜም ማንንም ሲገድሉ ደንታ የላቸውም ። አባቱ ዳኛ አባቱ ነፍጠኛ ።

ማፊያዎች ለመቀጣጫ ይገድላሉ ። ወያኔዎችም እንዲሁ ያደርጋሉ ። አባቱ ዳኛ አባቱ ወንጀለኛ ።

የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ አዳብረውታል ይባላል ፤ ቢዳብር ተጠቃሚው ማነው? አባቱ ዘራፊ አባቱ ገፋፊ ።

ወያኔዎች የአዲስ አበባን መልክ እንደለወጡት በሰፊው ይወራል ። እንዴት እንደለወጡት ግን በጠባቡም እንኳን አይወራም ። ለምሳሌ የከተማ ባለቦታ ፎቅ ቤት ለመሥራት አቅም እንደሌለው እያወቁ በቦታህ ላይ ወይ ፎቅ ሥራበት ወይም ለቀህ ሂድ ይሉታል ። ተገድዶ ለቆ ሲሄድ በሱ ቦታ ላይ ማነው ፎቅ ቤት ሠርቶ ኪራይ የሚሰበስበው?

ለውጡ የሚታየው አዲስ አበባ ላይ ብቻ አይደለም ። ከተሞች ሁሉ አቅኚዎቹ እየተነቀሉ በአዲስ ባለንብረቶች እየተያዙ ነው ።

ባንኮች የሚያገለግሉት ሥልጣኑን የያዙትን ማፊያዎች ነው ። ምሥጢር የሚያወጣ ዕለቱን ይጠፋል ። ጋዜጠኛ ከመንገድ ታፍኖ ይወሰዳል ። ዜና ከውጪ እንዳይገባ መንገዱ ሁሉ በእሳት ታጥሯል ።

ፕሬዚዴንት ኦባማ ስለማፊያዎች ማንም ሰው ሊያውቅ የሚችለውን ያህል እንደሚያውቅ አልጠራጠርም ። ኢትዮጵያን ወጥረው የያዟት ዲክታተሮች እንጂ ማፊያዎች መሆናቸውን ግን የጠረጠረ አይመስለኝም ። አማካሪው ጠበቃቸው ናት ። ገንዘብ እንደሁ አከማችታችኋል ሲል ፥ ማፊያዎች የንብረት ጣሪያ እንደማያውቁ አጥቶች አይደለም ። ገንዘብ እንደሁ አከማችታችኋል ምንጩን ለሌላ ልቀቁ ሲል አንድ ማፊያ የገንዘን ምንጩን ለሌላ ማፊያ እንደማይለቅ አጥቶት አይደለም ። ቢለቁም እንኳን የምንፈልገው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና ነፃ የሆነ ሕግ አስከባሪ እንጂ ምንጩ ላይ ቦጥቧጭ ማፈራረቅ አይደለም ።

ፕሬዚዴንት ኦባማ መሪዎቹን ልክ ልካቸውን የተናገራቸው መስሎታል ። መልሰው እንዳሞኙት ልብ አላለውም ፤ አጨበጨቡ ። አሾፉበት ። ቀለዱበት ። እሱ ግን ያጨበጨቡለት መስሎታል ። የኢትዮጵያው የዘንድሮው ምርጫ ዲሞክራሲያው ነው ያለ ጊዜ ፥ የሚናገረው ሚዛን እንደማያነሣ እንደታዘቡት አላወቀም ። መሬቱንና ንብረቱን ለሚዘርፍ ፥ ሀገሩን ለሚሸጥ ፣ በዘር የበላይነቱን በየዕለቱ ለሚያስታውቅ ቡድን መቶ በመቶ ድምፅ የሚሰጥ የየትኛው ክፍለ ሀገር ሕዝብ ነው-- የጎጃም ነው ፥ የጎንደር ነው ፥ የወሎ ነው ፥ የአርሲ ነው ፥ ወይስ የሸዋ?

"አደባባይ ወጣሽ ፤ ምን አመጣሽ?" ይላል ያገሬ ሰው ቀኑን ሙሉ አደባባይ ለአደባባይ ተንቀዋላ የተመለሰችውን ሚስቱን ሲወቅስ ። ፕሬዚዴንት ኦባማ ስለአፍሪካ ጉዞው ቢጠየቅ "ዘመዶቼን ጠየቅሁ ፤ ስሜን አስነሣሁ ፤ በሺ የሚቆጠሩ አሜሪካኖች ሲያጅቡኝ ለዘመዶቼ አሳየሁ" ይል እንደሆነ ነው እንጂ ለአፍሪካም ሆነ ለአሜሪካ አንዳች ቁም ነገር አልሠራም ።